# ተመልሰን ወደ እግዚአብሔር ክብር ተዋጅተናል

# (We Have Been Redeemed Back to the Glory of God)

በአዲስ ኪዳን ውስጥ፥ በሚከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃልና በሌሎችም አንቀፆች፥ የእኛ "ድኅነት" ሦስት ነገሮች ይዞአል: 1) መጽደቅ (justification) ፥ 2) መቀደስ (sanctification) ፥ እና 3) መክበር (glorification) ። ወደ መክበር የምንሄድበት ብቸኛው መንገድ መቀደስ ነው። "መጽደቅ" ላይ መቆም እና መቀደስን ችላ ማለት በክርስቶስ ካለን ከዘላለማዊ አላማችን ራሳችንን ውድቅ ማድረግ ነው።

*እኛ ግን፥ በጌታ የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ፥ ሁልጊዜ ስለ እናንተ እግዚአብሔርን ልናመሰግን ግድ አለብን፥ እግዚአብሔር በመንፈስ መቀደስ እውነትንም በማመን ለመዳን እንደ በኵራት መርጦአችኋልና፤*

*ለዚህም የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር ለማግኘት በወንጌላችን ጠራችሁ።* **2ኛ ተሰሎንቄ 2:13-14**

የእግዚአብሔር የዘላለም አላማ ከኃጢአትና ከኃጢአት ኃይል እጅግ በጣም የዳኑ ሰዎች ወደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መልክ ተለውጠውና ከእርሱ ጋር ከብረው እንዲኖሩት ነው። God's eternal purpose is to have a people who are so thoroughly saved from sin and its power that they are transformed into the image of the Lord Jesus Christ and are glorified together with Him. እግዚአብሔር ክርስቶስን የሚያውቁ፣ የሚያፈቅሩና በክርስቶስ የሚኖሩ ሰዎች እንዲኖሩት ይሻል፤ እርሱን(እግዚአብሔርን) እጅግ በጣም ከሁሉ በላይ አልቆ የሚያፈቅረው ሕዝብ እንዲኖረው ይሻል፤ የእርሱ ባሕርይ(ቅዱስ ፍቅር) ያለው ሕዝብ እንዲኖረው ይሻል በእነርሱም እርሱ ፍቅሩን፣ ፈቃዱን፣ ጥበቡን፣ ጸጋውን እና ኃይሉን ይገልጣል። የእግዚአብሔር አላማ(እቅድ) ለልጁ ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሙሽራ ማግኘት(እንዲኖረው) ነው። ይህ መቀደስና መክበር ይጠይቃል። God's plan is to have a bride for His Son, the Lord Jesus Christ. This requires sanctification and glorification.

እናንተንም ነውርና ነቀፋ የሌላችሁና ቅዱሳን አድርጎ በእርሱ ፊት ያቀርባችሁ ዘንድ፥ በፊት የተለያችሁትን ከፉ *ሥራችሁንም* በማድረግ በአሳባችሁ ጠላቶች የነበራችሁትን አሁን በሥጋው ሰውነት በሞቱ በኩል አስታረቃችሁ። 23 ይህም፥ ተመሥርታችሁና ተደላድላችሁ ከሰማችሁትም ከወንጌል ተስፋ ሳትናወጡ፥ በሃይማኖት ጸንታችሁ ብትኖሩ ይሆናል። ያም ወንጌል ከሰማይ በታች ባለው ፍጥረት ሁሉ ዘንድ የተሰበከ ነው፥ እኔም ጳውሎስ የእርሱ አገልጋይ ሆንሁ። **ቆላስያስ 1:21-23**

*ለሁሉም ሰዎች* የእግዚአብሔር ፈቃድ እያንዳንዱን አማኝ ቅዱስ እና እንከን የሌለበት ከነቀፋም በላይ አድርጎ በእርሱ(በእግዚአብሔር) ፊት ማቅረብ ነው። (ኤፌሶን 5:25-27፥ ቆላስያስ 1:28፥ ቲቶ 2:14)። ይህ ሊሆን የሚችለው:

1) በእምነት ተመሥርተንና ጸንተን ስንቆይ፥ እና

2) "የክብር ተስፋ ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ አለ" ከሚለው ከወንጌሉ ተስፋ ካልተናወጥን (ቆላስያስ 1:27) ብቻ ነው።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀዳሻችን ነው! (1ኛ ቆሮንቶስ 1:30፥ የሐዋርያት ሥራ 26:18)። እኛ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ባለን እምነት ድነናል (ጸድቀናል፣ ተቀድሰናል ከብረንማል)።

*ነገር ግን። "አመንሁ ስለዚህም ተናገርሁ" ተብሎ እንደ ተጻፈ ያው አንዱ የእምነት መንፈስ ስላለን፥ እኛ ደግሞ እናምናለን ስለዚህም እንናገራለን፤* **2ኛ ቆሮንቶስ 4:13**

እምነት ድምፅ አለው። እምነት ይናገራል።
*ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤ ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መስክሮ ይድናልና።* **ሮሜ 10:9-10**

**ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ልንመሰክር ነው።** እርሱ ማን እንደሆነ ልንመሰክር ነው፣ እርሱ ምን እንዳደረገ ልንመሰክር ነው፣ እርሱ ምን እያደረገ እንደሆነና ምን እንደሚያደርግ ልንመሰክር ነው። እግዚአብሔር እርሱን ከሙታን እንዳስነሣው ልናምንና እርሱን ልንመሰክረው ነው። We are to believe God raised Him from the dead and confess Him. እርሱ የክብር ተስፋ ነው።

በእምነት ጸንተን በመቀጠል (ምስክርነታችንን ጠብቀን በመያዝ(በመጠበቅ) ዕብራውያን 4:14 ፥ ዕብራውያን 10:23) እና በእኛ ካለው ከክርስቶስ ተስፋ ባለመነቃነቅ ወደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መልክና አምሳል እንለወጣለን!

## THE PAST TENSE of the GOSPEL according to Paul

### *መንፈስ ቅዱስ ወንጌልን በጳውሎስ እንደጻፈው*

**ኤፌሶን 1:4** ዓለም ሳይፈጠር፥ በፊቱ ቅዱስና ነውር የሌለኝ በፍቅር እሆን ዘንድ እግዚአብሔር በክርስቶስ መርጦኛል።
**ኤፌሶን 1:5** በበጎ ፈቃዱ እንደ ወደደ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ *ሥራ* ለእርሱ ልጁ(ወንድ ወይም ሴት ልጁ) ልሆን አስቀድሞ በጸጋው ወሰነኝ።
**ሮሜ 8:28-29** የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን መልክ እንድመስል በእግዚአብሔር አሳብ(አላማ) *መሠረት ነገር ሁሉ* ለበጎ ይደረግልኛል።

**ኤፌሶን 1:6-7** በእግዚአብሔር ተቀባይ ነኝ፥ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ተቤዠቻለሁ ኃጢአቶቼ በሙሉ ተሰርየዋልም። (ቆላስያስ 1:14)

**ቆላስያስ 1:21** ከእግዚአብሔር ጋር ታርቄአለሁ።
**ሮሜ 5:1** በእምነት ጸድቄአለሁ በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን ይዤአለሁ። (በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ጸድቄአለሁ አሁንም ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም አለኝ።)
**ኤፌሶን 1:11** ርስትን ተቀብዬአለሁ(አግኝቼአለሁ) : እግዚአብሔር ራሱ ብድራቴ ነው። የእርሱ መንግሥት ሁሉ በርስቴ ውስጥ ተካትቶአል(ተጨምሮአል)። (ራእይ 21:7፥ 1ኛ ቆሮንቶስ 3:22)
**ቆላስያስ 1:12** አብ በቅዱሳን ርስት በብርሃን እንድንካፈል አብቅቶኛል
**ቆላስያስ 1:13** እግዚአብሔር ከጨለማ ሥልጣን አዳነኝ፥ ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰኝ።
**ሮሜ 6:6-8** ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሲሞት፥ እኔ ከእርሱ ጋር ሞትሁ። አሮጌው ሰዌ ሞቶአል። My old nature was put to death.
**ቆላስያስ 2:12** በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀብሬአለሁ
**ቆላስያስ 2:11** የሥጋንም (የኃጢአት) ሰውነት በመገፈፍ፥ በክርስቶስ መገረዝ፥ በእርሱ ሆኜ ደግሞ ተገረዝሁ።
**ቆላስያስ 2:12** ከእርሱ ጋር ከሙታን ተነሣሁ..
**ቆላስያስ 2:13** ከእርሱ ጋር አሁን ሕያው ነኝ።
**ቆላስያስ 2:13** በደሎቼ ሁሉ ይቅር ተብለዋል።
**ሮሜ 6:6-7** ከእንግዲህስ ወዲያ ለኃጢአት የተገዛሁ(ባሪያ) አይደለሁም። ከኃጢአት ኃይል ነጻ ነኝ። I am no longer a slave to sin. I am free from the power of sin.
**ሮሜ 6:14** ክርስቶስ በእኔ ውስጥ ስለሆነ ኃጢአት አይገዛኝም (ቆላስያስ 1:27)፤ እኔም አሁን በእርሱ ኃይለኛና በሚለውጥ ጸጋው እየኖርሁ ነው (ኤፌሶን 2:8)።
**ቆላስያስ 2:10** በእርሱ ሆኜ ተሞልቼአለሁ። I am complete in Him.
**1ኛ ቆሮንቶስ 6:17** ከጌታ ጋር ተባብሬአለሁ። I am joined to the Lord.
**ቆላስያስ 1:27** የክብር ተስፋ ያለው ክርስቶስ በእኔ ዘንድ ነው። (የክብር ተስፋ ክርስቶስ በእኔ ውስጥ ነው።)
**ኤፌሶን 5:30** እኔ የአካሉ፣ የሥጋው እና የአጥንቶቹ ብልት ነኝ።
**ቆላስያስ 3: 3** ሕይወቴ በእግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ተሰውሮአል።
**ቆላስያስ 3:4** ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወቴ ነው አሁን።
**ፊልጵስዩስ 1:21** ለእኔ ሕይወት ክርስቶስ ነው።
**ዮሐንስ 6:57** ጌታ ኢየሱስ ከአብ የተነሣ ሕያው እንደሆነ፤ እኔም በእኔ ባለው በክርስቶስ ሕይወት አሁን እኖራለሁ። (ዮሐንስ 17:21)

**ፊልጵስዩስ 3:3** እኔ በክርስቶስ ኢየሱስ እመካለሁ(እደሰታለሁ) በሥጋም አልታመንም (በሥጋም መሥራት በምችለው አልታመንም)። “ እኛ በመንፈስ እግዚአብሔርን የምናመልክ በክርስቶስ ኢየሱስም የምንመካ በሥጋም የማንታመን እኛ የተገረዝን ነንና።”

**ገላትያ 2:20** ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው።

**ሮሜ 1:17** “ጻድቅ በእምነት ይኖራል” ተብሎ እንደ ተጻፈ የእግዚአብሔር ጽድቅ ከእምነት ወደ እምነት በእርሱ ይገለጣልና።
**ሮሜ 1:16** ይህ የክርስቶስ መልካም ዜና የምሥራች (ያም እኛ እርሱን(የእግዚአብሔርን ልጅ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን) በማመን የምንኖረው) ለሚያምኑ ሁሉ ለማዳን የእግዚአብሔር ኃይል ነው።

**መቀደሴ - MY SANCTIFICATION**

**2ኛ ቆሮንቶስ 1:21** በክርስቶስ ያጸናኝ እግዚአብሔር ነው።
**1ኛ ቆሮንቶስ 1:30** ቅድስናዬ(መቀደሴ) በተደረገልኝ በክርስቶስ ኢየሱስ መሆኔ ከእግዚአብሔር አድራጎት ነው።
**ፊልጵስዩስ 4:13** ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ።
**ፊልጵስዩስ 3:3** በክርስቶስ ኢየሱስ እመካለሁ(እደሰታለሁ) በሥጋዬም አልታመንም።
**ኤፌሶን 2:10** እኔ የራሴ ቀዳሽ አይደለሁም፥ እኔ “ፍጡሩ ነኝና፤ እመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርሁ።” እኔ የእርሱ ፍጡር ነኝ!
**1ኛ ቆሮንቶስ 1:30** ኢየሱስ ቀዳሼ ነው Jesus is my Sanctifier
**1ኛ ተሰሎንቄ 5:23-24** የሰላምም አምላክ ራሱ ሁለንተናዬን ይቀድሳል፤ መንፈሴም ነፍሴም ሥጋዬም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ያለ ነቀፋ ፈጽመው ይጠበቃሉ። የሚጠራኝ የታመነ ነው፥ እርሱም ደግሞ ያደርገዋል።

**ዕብራውያን 13:20-21** በዘላለም ኪዳን ደም ለበጎች ትልቅ እረኛ የሆነውን ጌታችንን ኢየሱስን ከሙታን ያወጣው የሰላም አምላክ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በፊቱ ደስ የሚያሰኘውን በእኔ እያደረገ፥ ፈቃዱን አደርግ ዘንድ በመልካም ሥራ ሁሉ ፍጹም ያደርገኛል፤ ለእርሱ እስከ ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን፤ አሜን።

**መዝሙር 138:8** እግዚአብሔር ብድራትን ይመልስልኛል + The LORD will perfect *that which* concerns me

**ፊልጵስዩስ 1:6** በእኔ መልካምን ሥራ የጀመረው እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ድረስ እንዲፈጽመው ይህን ተረድቼአለሁና፤
**ሮሜ 5:5** በተሰጠኝም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልቤ ፈስሶአል።

**ዮሐንስ 15:10-12** እርሱ(ኢየሱስ ክርስቶስ) የአባቱን ትእዛዝ እንደ ጠበቀ በፍቅሩም እንደሚኖር፥ እኔም የኢየሱስን ትእዛዛት መጠበቅ እችላለሁ በፍቅሩም እኖራለሁ። ደስታውም(የኢየሱስ ክርስቶስ ደስታ) በእኔ እንዲሆን ደስታዬም እንዲፈጸም ኢየሱስ ይህን ነግሮኛል። እርሱ(ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ) እንደ ወደደን እርስ በርሳችን እንዋደድ ዘንድ ትእዛዙ ይህች ናት።

**1ኛ ዮሐንስ 4:16** እኛም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር አውቀናል አምነንማል። እግዚአብሔር ፍቅር ነው፥ በፍቅርም የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል እግዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል።

**ፊልጵስዩስ 4:13** ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ።

**ቆላስያስ 1:27** ክርስቶስ በእኔ ውስጥ የክብር ተስፋ ነው። Christ in me is the hope of glory.

**ፊልጵስዩስ 1:21** ለእኔ ሕይወት ክርስቶስ ነው። For me, to live is Christ.

**1ኛ ተሰሎንቄ 3:12-13** ክርስቶስ በእኔ ስለሆነ፥ እኔ የእርሱ ፍጡር ስለሆንሁ፥ እርሱ ቀዳሼ ስለሆነ፥ በእግዚአብሔር ፊት በቅድስና ነቀፋ የሌለበት ሆኖ ልቤ እስኪጸና ድረስ ለሁሉም የሚሆን ፍቅሬ ይበዛልም ይጨምራልም (ለሁሉም ሰው በፍቅር እበዛለሁ እጨምርማለሁ)።

መራርነት፣ ቅሬታ እና ይቅር አለማለት በሕይወቴ ምንም ስፍራ የላቸም።

ሁከት(ጥል)፣ ክርክር(ጭቅጭቅ)፣ በራስ ያለ ከፍተኛ አመለካከት (ራስ ወዳድነት ego) ፣ ትዕቢት(ኩራት) እና ምኞት በሕይወቴ ምንም ስፍራ የላቸውም።

ዝሙት፣ ራስ ወዳድነት እና ስስት ከእግሮቼ በታች ናቸው።

በክርስቶስ በፍቅር ቅዱስና ያለነቀፋ ሆኜ ጸንቼአለሁ።

በመንፈስ ቅዱስ እየተዘጋጀሁ ነው እንደ ንጽሕት ሙሽራም ራሴን ለሙሽራው ንጉሥ ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዝግጁ እያደረግሁ ነው።

I am being prepared by the Holy Spirit and am making myself ready as a pure bride for the Bridegroom King, the Lord Jesus Christ.

http://www.shekinahworship.com/ , http://www.baptizingfire.com , http://fireofgodservants.blogspot.com/ , http://www.thelordshour.com , http://www.choothomas.org , http://www.jesusministries.org/ , http://www.angeltv.org , http://www.Billygraham.org , http://free.messianicbible.com/ , http://www.levitt.tv/ ,

http://www.divinerevelations.info/amharic , http://www.heavenvisit.com , http://www.tribulation-now.org , http://www.voe.org/ , http://www.sidroth.org , http://repentandpreparetheway.org/ , http://www.theblazingholyfire.com/ , http://www.thelastreformation.com , http://www.be4thefire.com/

http://www.bobjones.org/ , http://www.annarountree.com/ , http://www.beyondthephysicalrealm.com , http://www.shreveministries.org , http://www.blogtalkradio/tribulation-now , http://www.blogtalkradio/thelordshour, http://www.blogtalkradio.com/discoveringthetruth , http://www.e-sword.net/

**ክብር፥ ኃይል፥ በረከት፥ ምስጋና፥ ጥበብ፥ ማዳን፥ ግርማ፥ ቅድስና፥ ውዳሴ፥ አምልኮ እጅግ በከበረ ቅዱስ ዙፋኑ ላይ ላለ ለቡሩክ የእስራኤል ኃያል አምላክ የሠራዊት ጌታ፥ አንድ አምላክ ለሆነ ለእግዚአብሔር አብ ለእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ለመንፈስ ቅዱስ ይሁን አሜን። ማራናታ ጌታ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ የአብ ቃል የአብ ልጅ ቶሎ ና። ሃሌ ሉያ ክብር ለመንፈስ ቅዱስ ሃሌሉያ**

የእስራኤልን አምላክ ቅዱስ፣ ፍቅር፣ ኃያል ያሑዋሕ እግዚአብሔርን የሚያመልክ፥ በሥጋ የተገለጠውን ከቀራንዮ መስቀል መከራ በኋላም ሞቶ በሦስተኛው ቀን ከሞት የተነሣውን፥ አሁንም በእግዚአብሔር አብ ቀኝ በክብር ያለውን፥ በክብርም እጅግ በቅርቡ የሚመጣውን አልፋና ኦሜጋ መጀመሪያና መጨረሻ ትንሣኤና ሕይወት መንገድና እውነት የሆነውን የእግዚአብሔርን ልጅ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኙን የሚያምን የሚያፈቅር የሚያገለግልም፥ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ደም የተዋጀ፥ በመንፈስ ቅዱስም የተቀደሰ፥ የእግዚአብሔርን አሳብ በክርስቶስ ኢየሱስ ጸጋ፣ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት እያገለገለ ያለ፥ በጌታ ኢየሱስ የመስቀል ላይ ሥራ የሚመካ የሚደሰትም በጌታ ኢየሱስም በቅድስና የሚኖር፥ የጌታውን የኢየሱስ ክርስቶስን የያሑሹዋን ትእዛዝ የሚጠብቅ የሚያደርገውም፥ የሠራዊት ጌታን ሕያው እግዚአብሔርን የሚያከብር የሚፈራም፥ የእግዚአብሔርን ቃል ዕለት ዕለት የሚያሰላስል፥ ለአብ ፈቃድ የሚኖር በፍቅሩም የሚተጋ፥ የክርስቶስ ኢየሱስን መንፈስ የሚያዳምጥ በትሕትናም ለጸጋው ቃል የሚታዘዝ፥ ሊያደርግ የሚገባውን ያደረገ፥ የማይጠቅም ባሪያ ተረኅመው። ክብርና ምስጋና ኃይልና ሞገስ ፍቅርም ከዘላለም እስከ ዘላለም ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ለሆነ ለሕያው በረከት ለ**እግዚአብሔር** ይሁን።

# ሃሌ ሉያ!!! ክብር ለታረደው የእግዚአብሔር በግ የእግዚአብሔር ቃል የነገሥታት ንጉሥ የጌታዎች ጌታ ለናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ይሁን አሜን ሃሌ ሉያ አሜን ሃሌሉያ አሜን ሃሌ ሉያ